# ሀ ሁ ፖለቲካ--ትላንትን ረስቶ ነገን ፍለጋ!

*ሀማ ቱማ*

አለመታደል ሆነና ሀቅ ያንቅ ነውና ነጋ ጠባ ሀቁ ሲነገር የሚያማቸውና አልፎም አንቆ የሚያስጓ
ራቸው ጥቂቶች አይደሉም፡፡ ሂስና ወቀሳ ስድብ እየመሰላቸው ለምን ተደፈርን፤ ክቡራን የፖለቲ
ካ ጣዖቶችን እንዴት ደፍራችሁ ተቻችሁ በሚል የሚያወግዙን፤ የተተቹት በጠላትነት የታዩ
መስሏቸው ኡኡ የሚሉ ግን ሀቁ ሲመረመር ደግሞ የፖለቲካ አልፋና ኦሜጋን አጣጥመናል ቢሉ
ም ገና የፖለቲካ ሀሁን ያልቆጠሩ መሆናቸውን -ተወደደም ተጠላም-- መናገሩና መፃፉ የሚታለ
ፍ አልሆነም፡፡ በበኩላችን ትግል ብለን ስንጀምር ጣዖትን ማንኮታኮቱ ግዳጅ ነው ብለን የተነሳን
በመሆናችን ጫጫታው እምብዛም አላወከንም፡፡

ብሬት ቢንጫጫ መድፋቸው ቢያጓራ
ለምን ይደክማሉ እኔ እንደሁ አልፈራ

ያለውን አርበኛ እናስታውሳለን እንዲያውም፡፡

ወያኔ ከተቃዋሚው የበላይ መስሎ ለመታየትና በስልጣንም ለመቀጠል የቻለው ከሞላ ጎደል
የፖለቲካውን መድረክ በቁጥጥር ለማስገባት በመቻሉና የፖለቲካውን ትኩረትን በተመለከተም
ቃኚ እኔ ነኝ ብሎ መሰየም በመቻሉ ነው፡፡ ወያኔ ይህን ለማድረግ በቅድሚያ የራሱን ግብ ጠንቅ
ቆ ከማወቁ ሌላ ጠላት ያለውን ሕዝብና ድርጅቶችንም በተመለከተ ምን ማድረግ እንዳለበት
በመረዳቱ ነው፡፡ የኢትዮጵያን ሕዝብ በአብዛኛው ጠላት ብሎ በመፈረጁ ገና ከደደቢት ጀምሮ
የጠነሰሰው ፖለቲካ ከፋፍለህ አዳክም--ግዛ ነውና ለስልጣን ሲበቃ የክልልና የአንቀፅ 39ን ፖለቲ
ካ አሰፈነ ፡፡ ለሆዳቸው ና ለስልጣን ፍርፋሪ የሚያድሩትንም አውቆ በዚሁ መልክ ገዛቸው፡፡
አንድ አዛውንት ፕሮፌሰር እነ መለስን ልጆቼ ብለው በሎንዶን ስብሰባ ድጋፍ መስጠታቸውንም
የምንረሳው አይደለም፡፡ በሰኔው 83 ጉባዔም በፈረደበት አማራ ላይ ሲደነፉ--ከፕሮፌሰር አሥራ
ት በስተቀር-- የተሰበሰቡት ሁሉ አብረውት አጓሩ፡፡ የሚሾሙት ተሾሙ፤ ወንበር ብጤም ተሰጣ
ቸው፡፡ ወያኔ ማራቅ ያለበትንም ያውቅ ነበርና አይገዙልኝም ያላቸውን ደግሞ አሳደደ፤ ገደለ፤
ደብዛ አጠፋ፤ ህገ ወጥ ብሎ አገደ ፡፡ በጫት ቃሚነት ቢታማም መለስ ዜናዊ ሕዝብ ይወደኛል
በሚል አጉል ቅዠት ለደቂቃም ቢሆን ባለመሸነፉ “ ሕዝብን መግዛት በፍጅት” በሚል አፈናውን
ም አላልቶ አያውቅም፡፡ በዚህም መሰረት ብልጣ ብልጡ ወያኔ ተቃዋሚን እየከፋፈለ፤ የተቃዋሚ
ን ትኩረት ከዋናው ነጥብ ወደ መለስተኛው (ድምፃችን ተቀማ መሆኑ ቀርቶ የታሰሩት ይፈቱ
ለምሳሌ) እያደረገ ቀጥሏል፡፡ ለምሳሌ ወያኔን በትጥቅ ገና ከመጀመሪያው መፋለም ሲገባ የሰላም
ትግል ወይስ የብረት ትግል የሚል አጓጉል ክርክር ከፍቶና አስከፍቶ ዱላ አታንሱ መላ ይሻላል

ባዮችን ኮልኩሎ ሲያደናግር፣ ሲከፋፍልና ሲያደናቅፍ ታይቷል። ዛሬም ዋናው የትግል መፈክር ወያኔን ከስልጣን በአስቸኳይ ውረድ መሆኑ ቀርቶ በይስሙላ የምርጫ ጋጋታ መጠመድን ( ያው ም ወያኔ ይሸነፋል በሚል ቅዠት አምኖ መሳተፍን) አስፍኗል። በየታሪክ ማጠፊያ ላይም ቁም ነገሩ አልጫ እየሆነ ትላንትን እየረሳን ነገን መቀማት ዕጣ ክፍላችን ሆኖ ተሰቃይተናል። የ 66ቱ፣ የ83ቱ ይቅርና የ1997 ተዘንግቶ እነሆ በ2002 ስህተትን ለመድገም የተነሱትን መታዘብ ግድ ሆኗል።

በየጊዜው ተቃዋሚ ሀይሎችን የምንተቸው ወያኔ በራሱ ድክመት እየተሸረሸረ ባለበት ከውድቀት የሚድነው በራሱ ጥንካሬ ሳይሆን በተቃዋሚዎች ድክመት መሆኑ ተደጋገሞ የተነገረና ትክክል ም ግምገማ በመሆኑ ነው። ጠጣሩ እንዲላላ የላላውን ወጥር ነውና መሰረታዊው ምክር ተቃዋሚ ሀይሎች ድክመታቸውን አስወግደው እንዲጠናከሩ መተቸታቸው ተገቢ ነው። ድክመት ስንልም በቀቢፀ ተስፋ ተይዘውና ጨለምተኛነትን ጌታ አድርገው ትግሉ ገና ሳይፋፋም የደከሙት እንደ ሚሉት ሁሉም ከንቱ ነው ለማለት ሳይሆን የድርጅቶችን ጥንካሬና የማይካድ አስተዋፅዖ በግምት ይዘን ግን እየጎዳ ያለውን ድክመት በመጥቀስ መወገድ አለበት የሚለውን መልዕክት ለማስተላለፍ ነው። የ1997 ቱ ምርጫ ውጤት የተፈለገውን ግብ ባይመታም የታገሉት ድርጅቶች (ቅንጅትና ህብረት) ያደረጉት አስተዋፅዖና ጥረት በቀላሉ የሚገመትና በስህተትና ድክመት ደረጃ ብቻ የሚፈረጅ አለመሆኑም መታወቅ ያለበት ነው። ዛሬም ቢሆን በክህደት ጎዳና ተሰማርተው ከወያኔ ጋር በተለጣፊነት የሚሰሩትን ስናወግዝ በፖለቲካው መስክ ስህተት የሚፈፅሙትን ሆነ በምርጫ ው በመሳተፍ የሆነ ውጤት እናመጣለን ብለው የሚጥሩትን በጅምላ ማውገዙ ከዓላማችን ውጭ ነው። የድርጅቶች ሁሉ ጠንካራ ጎናቸው ወያኔን እያናጋው ነውና ወያኔ ጠንካራ ነው ሀገሩን ሁሉ ተቆጣጠረው ብሎ መላቀሱ ስህተት ይሆናል። ያለውን ተጨባጭ ሁኔታም አለመገምገም መሆኑ ም ግልፅ ነው። ነገሮችና ሁኔታዎችን በሚዛን ማየት ያሻል። በዚህ መሰረትና አጥር ክልል ውስጥ ም ነው ትችት ለማቅረብ የሚሞከረው። የፖለቲካ ንቃት በደከመበት ደግሞ አሉባልታና ጥራዝ ነጠቅነት ይሰፍናል። የፖለቲካው መድረክ የጨረባ ተስካር ሆኖ ይዘባረቃል። ይህን ለማስወገድ ራሳችንን መገምገሙና መተቸቱ አስፈላጊ ነው። የላላውን ለመወጠርና ጠጣር ነኝ ባዩን ለማላላት --ወያኔን ለማሸነፍ።

ከወያኔ ተፃረው የቆሙት ሀይሎች ሲጠቀሱ ግን ስህተትን ነጋ ጠባ የሚደግሙት ተመክሮ ጠፍቶ ሳይሆን እቅጩ ሲነገር የፖለቲካን ሀሁ መጨበጡን ሆነ ከተመክሮ መማርን አሻፈረን ስላሉ ብቻ ነው ብንል ማጋነን አይሆንም። ነገ ግንቦት 23 ያልተጠበቀ ሁኔታ ከተከሰተም የድርጅቶቹ ዝግጅትና የተነሱ -አምፁ ጥሪ ሳይሆን እንደ 1997ቱ በሕዝብ በራሱ ቁጣና መነሳሳ ት ምክንያት የሚከሰት ነው። በመጪው ምርጫ መሳተፍ ከድክመትና ስህተት አየተቆጠረ ያለው ይህን ሂደት ተቃዋሚዎች የሚጓዙበት ወያኔን ለማጋለጥና ሕዝብን ለማደራጀት መጠቀሚያ ይሆናል በሚል ሳይሆን በምርጫው በመሳተፍ ለውጥ ይመጣል ብለው አማኞች በመሆናቸው

ነው:: ተቃዋሚ ሀይሎች ጠላትና ወዳጅ ማነው በሚለው መሰረታዊ ጥያቄ ላይ ተገቢው አቅዋም ኖሯቸው በስራ ና ስምሪት ክፍፍል ደረጃ አንተ አንቺ በህጋዊው መድረክ ሌላው ደግሞ በሁለገቡ ብለው ቢሰማሩ ኖሮ --ማለትም ሁሉም ወያኔ ፀረ ሕዝብ አገዛዝ ነው ብለው አምነውና በመውደቁና መወገዱ አስፈላጊነት ተስማምተው በነበር - ምርጫውን ይበልጥ ወያኔን ለማጋለጥ መጠቀሚያ ማድረግ በተቻለ ነበር:: ይህ ግን አልሆነም:: የፖለቲካው ሀሁ ግድ የሚለውን ትምህ ርት መማር አቅቷቸው የተገኙት ክፍሎች ግን ከመደራደር በፊት የመደራደሪያ ዕቅዳቸውን አጋልጠው፤ ራሳቸውን ለጥቃት ሰጥተው፤ያረመኔ ልቡ ቀጋ መሆኑን ዘንግተው በወያኔ ተደናግረ ው፤ ከደጋፊዎቻቸው ተነጥለው/ተጣልተው፤ ወዳጅ ብለው ያልሆነውን አቅፈው ጉዞ ሳይጀምሩ እየተደናቀፉ ሲወድቁ አይተናል::

ምሳሌ፤

- ሁሉም የፖለቲካ እስረኞች ማለት ሲገባ ይፈቱ የምንለው የራሳችንን ብቻ ነው ይፈቱ የምንለው በማለት፤
- ወይም ከኢሕፓ ውስጥ ብቅ ያሉ አንጃች እንዳሉት የፖለቲካ እስረኞችን ጥያቄ " በኋላ እንጂ ዛሬ ማንሳት የለብንም" ብሎ ከሩቁ በመጎንበስ፤
- የፖለቲካ ድርጅት መሪ በህገ ወጥ መንገድ ታስራ እያለች ተፈታች ታሰረች ምርጫ እንገ ባለን ብሎ በመማልና ለድርድር እንኳን ባለመግደርደር፤
- ምን ተይዞ ጉዞ ወይም አፈ ወሪሳ እንዲሉ በገዋ--በባዶ ደንፍቶ ጠላት በማብዛት፤
- የሀገራችንን የአካባቢ ሁኔታና ዓለም አቀፉንም ሁኔታ ባለማጤን ያለውን አደጋ ለመገንዘ ብ ባለመቻል አቦ ሸማኔው እየመጣ ቀሪ ጥይትን በጥንቸል ላይ በመጨረስ፤
- ትጥቅ ትግል የጀመሩትን ከወያኔ በፊትና በላይ ማውገዝ፤
- ታግሎ ለሀገር መሰዋትን በጅልነት በመፈረጅ፤ የተሰዉትን ማብጠልጠል፤
- ትላንት የመሪነት ብቃት የሌላቸው መሆናቸውን ያረጋገጡትንና ሕዝብን የከዱትን ዛሬ መሪ ነፃ አውጪ ብሎ ማቀፍ፤
- ወያኔ ማንነቱን ከምርጫ አንፃር በ1997 አሳይቶ ያኔ የገደላቸው ወገኖችን ደም ሳንበቀል ና ያኔ የታሰሩት ዛሬም በየጉድጓዱ እየተሰቃዩ ባለበት አለ ተገቢና በቂ ቅድመ ሁኔታ በምርጫ ለመሳተፍ መሯሯጥ፤
- ምርጫ በመግባት የወያኔን ዕድሜ እናሳጥራለን ብሎ መቃዠት፤ ወዘተ የታዩት ሁሉ

የሚጠቀሱ ናቸው:: በዚህ ገፅ በርካታ የተቃዋሚ ድርጅቶች መሪዎች በየጊዜው በሰጡት መግለ ጫ የተጋለጠ ነውና መድገሙ አስፈላጊ አይሆንም:: በባዕድ ሀገር ያለው ደግሞ አላፊ አግዳሚው ለጆሮው የሚስማማ ከበሮ ሲደልቅለት ምራኝ-ምራን ብሎ መነጠፍና መታለል ጠባዩ እየሆነ መምጣቱ በመጠቀሱ ያው ውርጅብኝ ቢከተልም ሀቅ ሀቅ ነውና መነገሩ ግን አስፈላጊ ነው :: የፖለቲካ ሀሁ ጠላትህን ወዳጅህን በቅድሚያ እወቅ ይላል:: ወያኔ ጠላቶቹን ያውቃል::

ኢትዮጵያና ሕዝቧ ጠላቶቹ ናቸው:: አንዳንዶቹ ተቃዋሚዎች ግን ወያኔ ወዳጃቸው ይመስላቸዋል:: አንዳንዶቹ እንዲያውም ተቃዋሚ አትበሉን ወያኔዎች ወንድሞቻችን እህቶቻችን ናቸውና ተፎካካሪ ነን ይሉናል:: ወያኔ ጠላት ነው ስንል አሮጌ ፖለቲካ ነው፤ ሰልጥኑ ብለው ይወርፉናል:: መሰልጠኑ ጫንቃን ለባርነትና ለውርደት ማመቻቸት ሆኖብን ከበደን ብንላቸው አይገባቸውም፡ ተዋደዱ የሚሉ ነገር ዓለሙ ያልገባቸው ዘፋኞችም አሉ:: ቀለበት መንገድ፤ ፎቆች፤ቪላዎችን እዩ፤ አርሶ አደሩም የእጅ ቴሌፎን ይዟል፤ እናንት በታገላችሁበት በቋራ ሳሊያ ወይም ቴድሮስ ከተማ ሳይቀር እኮ ቴሌፎን ገብቷል ብለው ይገስፁናል:: ምን ማለት ነው ይህ ሁሉ 14 ሚሊዮን ሕዝብ በተራበበት ሀገር፤ 35 ሺ በላይ በታሰረበት ሀገር፤ መብት በተረገጠበት ሀገር፤ የህግ የበላይነት ባልተከበረበት ሀገር፤ ዘረኝነት በሰፈነበት ሀገር፤ ጭቆና በከፋበት ሀገር ስንላቸው መልስ የለም:: ለነሱ ለጥቂቶች አምሯልና ለእኛ ማስቀየሙ አይረዳቸውም:: ህሊና ደግሞ ከተሰናበተ ጊዜ አልፏልና የብዙሃኑ እንባና ሰቆቃ በሆድና ጥቅም ታፍኗል:: ነጋ ጠባ ኤኮኖሚው አደገ ተመነደገ የሚሉን ይህ ሁሉ ሚሊዮን ሕዝብ እንዴት ለረሀብና ለከፋ ድህነት እንደተጋለጠ አይናገሩም::ሆደና ዘረኝነት ከትቢያና ውርደት ጥሏቸዋል:: የፖለቲካ ሀሁ ከተማርን ግን በቅድሚያ ተጨባጩን ሁኔታንም ጠላትንም ማወቅ ወሳኝ ይሆናል:: ማወቅ ማለት ደግሞ ይዘቱን፤ ጠባዩን ድክመት ጥንካሬውን ማለት ነው:: በሌጣ ትንተና ማብቃት አንገደድም:: ወያኔ ከተመሰረተ ጀምሮ ስለዚህ ከይሲ ቡድን የተባለውን አልሰማንም ብንል እንኳን፤ ስልጣን ከያዘ ወዲህ የፈፀመውን ወንጀል ረሳን ብንል እንኳን፤ አደባባይ ኢየሱስን፤ አንዋር መስጊድን፤ወተር አርባጉጉን፤ጋምቤላን አጋዴንን ሕዝብ መጨፍጨፉን ወዘተ፤ ማን ፕሮፌሰር አሥራትን፤ አሰፋ ማሩን፤ተስፋዬ ታደሰንና ሌሎችን እንደገደለ ማንም አልነገረንም ብንል እንኳን፤ ትላንት በ1997 ስንቱን ንፁህ ዜጋ የጨፈጨፈውን ወያኔን አናውቀውም ማለቱ ሊፈቀድልን አይችልም--ሆዳችን ህሊናና አንጎላችንን አንቆ ካልገደለ በስተቀር::

የፖለቲካው መድረክ የተጨናነቀው የፖለቲካን ሀሁ በማያውቁ ግና ራሳቸውን ምሁር ፤"ልሂቅ" ዶክተር-ፕሮፌሰርና መሀንዲስ የሳይንስ አዋቂ በሚሉ ነው:: እነ አጅሬን ደግሞ ለስለስ ብሎ መናገሩም ክብረ ነክ ከሆነ ውሎ አድሯል::በምሁሮች መቅናት ነው ያሉም አሉ---ግን ሀቁን ተናግሮ የመሸበት ያድሯል ነውና አወቅን ባዮች ሰፊውን ሕዝብ ንቀው ሲውገረገሩ እየደረሰ ያለው በደልና ጉዳት መጠቀሱ አስፈላጊ ነው:: ሕንፃ ግንባታና ፖለቲካን፤ከብት ህክምናና ፖለቲካን፤ መሀንዲስነትና ፖለቲካን፤ ቀዶ ጠጋኝና ፖለቲካን፤ ወዘተ ምን እንዳቆራኛቸው ማስረዳት ከባድ ነው--ቀጥታ ግንኙነት የለምና :: ዛሬ ሚቹ ታዋቂ ዘፋኞችንና የወያኔ ወዳጅ አረባዊ ነጋዴም የክብር ዶክተር ቢባሉም ሚሊዮኖች ይህ ከስም ቀጥሎ የሚለጠፍ ነገር ስለሌለን ተለጣፊው ባላቸው ተንቀን ልሂቅ ዶክተር የሚባለውን አጨብጭባችሁ ተቀበሉ እየተባልን ነው::ፖለቲካ የጡረታ ጊዜም መዝናኛ ሆኗል:: ለረጅም ዓመታት ከፖለቲካው ርቀው የግል ኑሮአቸውን ሲያሳድዱ የቆዩት ድንገት ብልጭ ሲልባቸው ደግሞ ወደ ፖለቲካው መለስ ይሉና እኛ የተሳልን የተለጠለጥን ፖለቲከኞች የምንለውን አድምጡ ብለው ያተክሩናል:: ሌሎች ደግሞ ወያኔ ጋ ሄደው ደፋ

ቀና ብለው፤ ቆሻሻና ዘረኛ ጫማን ስመው መሬት ሊመሩ፤ ንግድ ፍቃድን ሊያገኙ በወገንና ሀገር እንባ ላይ ሊከብሩ ሞክረው ሲከሽፍባቸው ተመልሰው አለምንም ፀፀትና ይቅርታ የሕዝብ ወገን ነን ብለው የሚጮሁና በዚያውም ጥፋታቸውን እየደበቁ ያሉ አሉ:: ትላንት በአዲስ አበባ ሼራተ ን አስረሽ ምችው ነገ በዋሽንግተን ዲሲ መሰለፍና ይውደም ባይነት ብዙ አያዋጣም:: ይባስ ብሎ ደግሞ ትላንት ከመለስ ዜናዊ ጋር ሆነው ሀገር ወዳድ ዜጎችን ያጠፉ፤ ታጋይ ወገኖችን የገደሉ፤ በወያኔ ወንጀል የተካፈሉ ዛሬ ከግለሰብ መለስ ጋር ተጋጨን በሚል ሕዝባዊ ሆነናልና መሪያችሁ ነን ሲሉ እልል የሚሉ የፖለቲካ ሀሁ ያልገባቸውም በርክተዋል:: ግለሰቦቹ ሕዝባዊ ለመሆን በቅ ድሚያ ዘረኛውን የወያኔ ፖለቲካና መስመር ፀረ ኢትዮጵያ ብለው ማውገዝና ኢትዮጵያዊ ፖለቲ ካን በግልፅ መቀበል ይኖርባቸዋል:: ደብዛቸው የጠፉ የፖለቲካ ድርጅቶች መሪዎችና አባላት የት ደረሱ ሲባል አናውቅም ማለቱ ፍሬ ቢስ ነው--ወያኔ ስንል መለስ ዜናዊ ብቻ  አለመሆኑን እናውቃለንና! በወንጀል የተሳተፈ ግለሰብ ከሁሉም በፊት ንሰሐ መግባት አለበት:: ይህ ባልሆነበ ት ገዳይን ነፃ አውጪ ብሎ መቀበል ወያኔን ነፃ አውጪ ብለው የተቀበሉ የፈፀሙትን ስህተት መድገም ይሆናል:: ስህተቱን ነጋ ጠባ ለሚደግም ደግሞ ብዙዎች የሚያዝኑለት አይሆንም:: በሌላ በኩል ደግሞ የሞትን ክፉነት በቅድሚያ የሚያውቀው ሟቹ ነው እንደተባለው መከራና ሰቆቃው ያልደረሰባቸው ሁሉን ቻይ መሀሪና ይቅር ባይ መስለው ቢሰየሙ የሚገርም አይደለም:: እሳቱ አልጠበሳቸወምና ነው:: ወያኔ ወንድም እህት ጓዳቸውን አልፈጀባቸውምና ነው:: ምን አጠፉ ሲሉ ወይም በሰማዕት ላይ ሲሳለቁና ሟቾቹን ሲወቅሱ ማለትም በቁስላችን የጋለ ብረት ሲያስገቡ ችግራቸው አለመቁሰላቸው ነው:: የሰው ቁስል አይነዝርም ሆኖ  ነው! እስቲ እንጠያያቅ፤

የሌሎቹ ይቅርና ወጣት ሽብሬ ለምን ሞተች? የነአበራሽ ይቅርና ብርቱካን ለምን ታሰረች? በወያኔ እስር ቤት አለፍትህ የሞቱት ይረሱና፤ በቀይ ሽብር የተገደሉት መገደላቸውም ይካድና በ1997 በገፍና በግፍ የተረሸኑትስ ከ 200 በላይ ዜጎች?ጋምቤላ? አደባባይ ኢየሱስ? አሰቦት? ምስራቅ ወለጋ? ወተር? አንዋር መስጊድ? ኦጋዴን? ለምንስ የምናስታውሰው ሁሌም ጎዶሎና ያልተሟላ ይሆናል? ለምንስ ወንዝ ሊወስደን ሲል ቁጤማ መጨበጥ ይቀናናል? ለምንስ ጀግኖቻ ችን ብለን ልንመካባቸው የተነሳንባቸው ግለሰቦች ታሪካቸው የዝንጀሮ መቀመጫ ወይም አስቀያ ሚ ሆኖ ያስቸግራል? አስመሳይ ነፃ አውጪዎችን ያብቡ ባዮች አፉቸውን በእሬት ሊያጥቡ አይገ ባምን? ዛሬ ንስሐ ያልገቡ ወያኔዎችን እያዳነቁ ተቀቡሉ የሚሉንስ ለመሆኑ ህሊናቸውን መርምረ ዋል? ክህደቱ ስርየቱ ለምንስ ይሆናል? የአንዴው አይበቃም? በግ እንኳን ቢ ይላል የተባለው ተዘንግቶ ለወንጀላቸው እባካችሁ ማሩን አጥፍተናል የማይሉና ይባስ ብለው የተፈፀመውን ወንጀ ል አልተፈፀመም የሚሉ እንዴትስ የሕዝብ ነፃ አውጪ ይባላሉ? ከሁለተ መቶ ሺ በላይ ሕይወት ያጠፉን ሽብርና ሚሊዮኖችን ያቆሰለን ግፍ የሚክዱ እንዴትስ የፖለቲካ መሪ፤ ነፃ አውጪ ይባላ ሉ? ግፉ አልበዛም? ኃጢያት ሲደጋገም ፅድቅ ሆነብን?

ፖለቲካ ለምርጦች ወይም አንዳንዶች እንደሚሉት ለልሂቆች ብቻ ነው ባንልም ፖለቲካ ከባድ እንቅስቃሴ ነውና ዝግጅትና ንቃትን ይጠይቃል፡፡ በተለይ ድርጅትን አናንቀሳቅሳለን፤ ትግልን አጠናክረን ሕዝብን ለድል እናበቃለን ከተባለ ስምሪቱን እንደ ትርፍ ጊዜ ስራ መውሰዱና በቀላሉ መያዙ ፍሬ ቢስ ነው፡፡ ወያኔ ፖለቲካ የሙት ሽረት ጥያቄ ሆኖ ስለሚያስጨንቀው ሀያ አራት ሰዓት ሙሉ ግቡን ለማሟላት ተንኮል ሲሸርብ ፤ ሀሰት ሲያሰራጭ፤ ሲከፋፍል፤ ሲያስር ሲገድል ይታያል፡፡ አይተኛም ብንል ሁኔታውን ይገልጸዋል፡፡ ፖለቲካን በሙያተኛነት ይዞታል ማለትም እንችላለን፡፡ በመሆኑም ተፃራሪዎቹ ወይም ለሕዝብና ለሀገር መሰረታዊ ለውጥን እናመጣለን ብለው የተነሱ ወገኖች ፖለቲካን በጥራዝ ነጠቅነት ደረጃ፤ በአላዋቂ ሳሚነት፤ ልጅ የጫረው እሳት በመሆን፤ እንደ መዝናኛ በመቁጠር ይዘው ሊነሱ አይችሉም፡፡ የፖለቲካ ሀሁ ያልገባቸው ክፍሎች ጥላቻን ያወግዛሉ፡፡ ተዋደዱ ተፋቀሩን ይሰብካሉ፤ ነብር ፍየልን ሲያቅፍ፤ ጅብ አህያን ሲስም ይታያቸዋል፡፡ ቅዠት! ወያኔ በስልጣን የቆየው በሕዝብ ላይ ጥላቻውን በማርገ ገብ በማለስለስ ሳይሆን በማጠናከርና በማባባስ ነው፡፡ ትግል የራት ግብዣ አይደለም ተብሏል፡፡ ተቃቅፎ ወደድኩሽ ወደድኩህ መባባያም አይደለም፡፡ የሕዝብና የሀገር ፍቅር ለትግል ና መስዋዕ ተነትንም ለመድፈር መንስዔ ቢሆንም ትግል በጥላቻ ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ የጭቆና ጥላቻ፡፡ ጨቋኝን ጥላቻ፡፡ ጠላትን ወዶ ትግል የለም፤ ኖሮም አያውቅ፡፡ ሰላማዊ ትግል ተባለ ሌላ ጠላቱን ጠልቶ ያልተነሳ ወደ ድል አይጓዝም፡፡ በመሆኑም የወያኔን አገዛዝ ጠልተንና ልናወድመው ቆርጠ ን መነሳት አለብን ማለት ነው፡፡ የመለስ አገዛዝ በደም የተጨማለቀ ወንጀለኛ ቡድን ነው፡፡ መጠ ላት ሲያንሰው ነው፡፡ መንጌ መሉ የሚሉ ቀልደኞች ከፍርፋሪው የተቋደሱ ብቻ ናቸው--ያልደረ ሰባቸው፤ ያልቆሰሉ፤ ያልተጎዱ፡፡ የፖለቲካ ሀሁ ጠላትህን አውቅ፤ ጠላትህን ጥላ፤ ልታጠፋውም ቆርጠህ ተነሳ ይላል፡፡ ይህንን መሰረታዊ ሀቅ እየተቃወሙ፤ ጠላት አትበሉ፤ የሀገር ልጆች ነን ጠላቶች አይደለንም ወዘተ የሚሉ ሁሉ ትጥቅ አስፈቺና የባርነትን ቀምበር ላያችን ላይ አደላዳይ ናቸው፡፡ ቢወዱትም የማይወድ ስርዓት መሆኑን ሊሸፋፍኑ የሚጥሩ፡፡ ነጋ ጠባ የሚያዋርደንና የሚገድለን ስርዓት መሆኑን የሚዘነጉ፤ የተገደሉትንና የታሰሩትን ሁሉ የሚረሱ፡፡ ለዚህም ነው ተቃዋሚ ሀይሎች እንዋደድን ሳይሆን በጠላታችን ላይ አምርረን እንነሳን መስበክ ያለባቸው፡፡ ይህ ነው ተገቢው ፖለቲካ፡፡ ለዚህም ነው ቀስ በቀስ ወያኔ ህሊና ገዝቶ ይሻሻላል ማለትም መሰረ ተ ቢስ ሆኖ የሚገኘው፡፡ ለምርጫ ተብዬው ቀልድም ያን ያህል ገንዘብ መባከኑም አላግባብ ሆኖ የሚከሰተው፡፡

ቀደም ለማለት እንደተሞከረው የፖለቲካውን መድረክ ወያኔ በየጊዜው ዋና ጥያቄ ብሎ በሚያፈ ነዳው እያተራመሰ ዜጎችን ማደናገሩ እየቀጠለ ያለ ነው፡፡ የመወያያ የመጮኺያ ርዕስ ሰጪ ወያኔ ራሱ ይሆንና ዕይታችን ዋናውን ነጥብ ትቶ በመለስተኛ ጉዳዮች ላይ ያተኩራል፡፡ በ 1997 ምርጫውን አጭበርብሮና የሕዝብን ድምፅ አፍኖ ባለበት ህገ ወጥ ነህና ከስልጣን ውረድ የሚለው ን መፈክር የታሰሩት ይፈቱ በሚል እንዲሸፋፈን አደረገና ብዙዎች ዋና ተልዕኮአችን የታሰሩትን ማስፈታት ነው ብለው ሲጮሁ ቆዩ፡፡ አንዳንዶቹማ ይባስ ብለው ይህንኑም አጥብበው ይፈቱ

የምንለው " የራሳችንን" እስረኞች ብቻ ነው ብለው ራሳቸውን ለትዝብት ዳረጉ:: በቅሎው ተሰር ቆ ባረጀ ኮርቻ ላይ ኡኡታ እየሆነ መቸገራችን አልቀረም:: የድርጅትን ምንነትና ሚናም በተመ ለከተ ተገቢው ግንዛቤ ባለመኖሩ ፖለቲካ ያልነው መደነባበሩ አልቀረም:: ከአያሌ ዓመታት ውድ ተመክሮ በኋላ አሁንም ብቸኛ መሪ ድርጅት የሚለውን አጓጉል ንግግር አልተው እንዳሉ አሉ:: በ1997 ኡ ተመክሮ እንዳየነው አንድ ስብስብ እኔ እንጂ ሌላ ማን አለና ብሎ ሲኩራራና ትብብር ንም እምቢ ሲል የደረሰው ጉዳት የሚረሳ ሊሆን አይገባም:: ዛሬም አንድን ድርጅት ብቸኛ የሕዝ ብ ድርጅትና መሪ ብሎ ማቅረቡና በዚህም ተወስኖና ተቃኝቶ ሌሎችን ማክቸልቸሉ ጠቀሜታው ለወያኔ መሆኑን ገና ያልተረዱ አሉ:: የሀገራችን ዋና ዋና ችግሮች በአንድ ግንባር ቀደም ተብሎ በደጋፊዎቹ በተሰየመ ድርጅት ብቻ የሚወገዱ አለመሆናቸውን መረዳት ያቃታቸው አሉ :: ሁሉም ሀገር ወዳድ ድርጅቶች በየፊናቸው ሆነ በትብብር ሊያደርጉት የሚችሉት አስተዋፅዖ መኖሩንም ይክዳሉ:: አንዳንዶችማ መሪና ብቸኛ ድርጅት እገሌ ነውና ሌሎቻችሁ ፍረሱ አሊያ ም ከእሱ ተደባለቁ ብለው ይመክራሉ:: የፖለቲካ ሀሁ ገና አልተቀራም::

የግንዛቤ ማጠር ችግር ደግሞ ይቀጥልና የሀገሪቷ ዋና ዋና ችግሮች ምን ምን መሆናቸውም ራሱ ምስጢር ሊሆን ይከጅለዋል--ወይም ለብዙዎች ይሰወራል:: ሀገር ማዳን የሚለው ወቅታዊና ተገቢ መፈክርም ይዘቱ ይምታታና፣ ስፋቱም ይሳትና ወሳኝ የሀገራችን ችግሮች እንዳይነሱ በእን ቅፋትነት ማጠየቂያ ሆኖ ይቀርባል:: ተልዕኮአችን ሀገር ማዳን ነውና በሴቶች ላይ ስለሚደርሰው በደል፣ ስለ ጎጂ ባህሎች፣ ስለ መብት ረገጣዎች አታንሱ የሚሉ አሉ:: ግባችን ሀገር ማዳን ነውና በአንድ ድርጅት ጥላ ስር መሰበሰብ እንጂ ስለ ሴቶች መደራጀት ለምን ይወራል? ለምንስ ብዙ ድርጅቶች ይኖራሉ ወዘተ የሚሉ የተሳሳቱ አቅዋሞች መድረክ ላይ ብቅ ይላሉ:: ሴቶች ተደፈሩ ፣ መብታቸው ተረገጠ ፣ ውሁዳን ተሰቃዩ፣ ሰብዓዊ መብትም ተገረሰሰ፣ የህፃናት መብት ተደፈረ ወዘተ ሲባል ይህ ሁሉ ትርፍ ነው፣ ዋናው ሀገር ማዳን ነው ይላሉ:: ይህ ፖለቲካዊ ዕውቀት ሳይሆ ን የአለማወቅ ምልክት ነው:: የህብረተሰቡ ልዩ ልዩ ክፍሎች በየራሳቸው መደራጀታቸውና መብታቸውን ለማስከበር መታገላቸው (ለምሳሌ ሴቶች እንደ ሴቶች፣ ላባደሮች፣ ወጣቶች ወዘተ) ለትግሉ ስኬት ወሳኝ ሚና እንዳለው መሳት አይገባም:: የቅንጦት ጥያቄና መፈክሮች መስለው የሚታዩት ዓይኑ ለተጋረደ ብቻ ነው:: ሀገር ማዳን ሲባልም በቅድሚያ ሕዝብን ማዳን ማለትም የሕዝብን መብትና ሰብዕና ማስከበር ማለት መሆኑን መዘንጋት ስህተት ነው:: ሀቀኛ ሀገር ወዳዶ ችን ከወያኔ ዓይነት ብሄርተኞች የሚለየው አንዱ ዋና ጉዳይ ይህ ነው--ሕዝብን ማስቀደም ወይስ አደዬ/ብሔሬሰቤ/ጎጤ ማለት:: የወያኔ ሰለባዎች--አንዳንዶቹ ትላንት ኢትዮጵያዊ ነን ሲሉ የነበ ሩና ዛሬ ጠበው ወደ ጎጣቸው የተመለሱ--ሰፋ ያለውን ሕዘባዊና ሀገር ወዳድ አቅዋምን ትተው ወዲ ትግራይ ወዲ ትግራይን ወይም ሀፍረተ ቢሱ እንዳለው ወርቅ ዜጋ ነን ማለትን እስከቀጠሉብ ት ደግሞ የነገው መዘዝ በወርቅ ተብዬ ራሳቸው ላይ መውደቁ አይቀሬ መሆኑን ማወቅ ይገባቸዋ ል:: ጆሮያለው ይስማ፣ ጨው ለራስህ ብለህ ጣፍጥ ፣ ወያኔም ይወድምና ያስተዛዝበናል ይኸ ቀን ያልፍና ወዘተ ማለት ይቻላል::

የኢትዮጵያ ሕዝብ የናቁትን ሁሉ ሁልጊዜም የማይረሳ ትምህርት ሰጥቶ ለመስደዱ ጣሊያን ወይም ሐራሬ ድረስ መሄድ አይኖርብንም:: የኢትዮጵያን ሕዝብ ማንነት ግን አወቅን ባይ ዜጎች የዘነጉት ለመሆኑ ደግሞ ጥርጥር የለውም:: በአፋዊ ደረጃ አዋቂ ሕዝባችን፣ አዬው ይሉ እንደነበ ረው የሚወደንና የምንወደው ሕዝባችን ቢሉትም ሀቁ ግን አያውቅም አልተማረም፣ ምሁር አልሆነም ብለው ናቅ እንደሚያደርጉት ማመን አለብን:: ለዚህ ነው እናውቅልሃለን፣ የሰለጠነ ፖለቲካ ከእኛ ተማር ወዘተ ብለው የሚነዘንዙት:: ሕዝባዊ ምሁራን በምርጦችና ልሂቅ ተብዬዎ ች የተተኩ ቢመስለን ሊፈረድብን አይገባም ማለት ነው:: ሕዝብ የድል ባለቤት ነው፣ ሕዝብ የትግሉ መሰረት ነው፣ ሕዝብ አዋቂ ነው የሚባለውን ከልባቸው የማያምኑ ድርጅቶች ሕዝብን ከ ማደራጀት አንፃር ድክመት ያጠቃቸዋል:: የቀድሞ መሪዎች ሕዝብ ምን አለ፣ እረኛ ምን አንጎራ ጎረ ይሉ ነበር ይባላል--ዛሬ ይህ ደብዛው ጠፍቷል፣ ህዝብን ስማ ጎበዝ እንጂ ምን ትመክራለህ የሚለው ቁጥሩ አንሷል:: ከ 1997ኡ ምርጫ በኋላ  ታስረው የተፈቱት ሲፈቱ ወደ ሞተላቸውና ወደ ጮኸላቸው ሕዝብ ሄደው አመሰገኑ ወይስ ወዲያውኑ ወደ አሜሪካ ና አውሮጳ ተማረ ወደተ ባለው ነጎዱ? ዛሬስ ለምርጫ ተሰለፍን ያሉ የተወሰኑ ድርጅት መሪዎች ሚያዝያ እስኪያበቃ ይህ ንኑ በባዕድ ነዋሪ ሲቀሰቅሱ (ያውም ድምፅ ሳይሰጥ) አልቀዩም? ይህ በመሆኑም በባዕድ ሀገር ያለ ውዜጋም በሀገራችን ፖለቲካ ያለውን ሚናና ቦታ ግምት ሰቶ መገኘቱንም መታዘባችን አልቀረ ም::ሕዝብን የመናቁ በተለይም በወደቀው የፊውዳል አዬያዊ ስርዓት ጊዜ ሰፍኖ የነበረውን ይህን ውድቅ ስሜት የማስተጋባቱ አባዜ በመስፈኑ ድርጅቶች ሕዝብን አገልግል የሚለውን መመሪያ ዘንግተው ሕዝብን ተጠቀምበት የተባሉ ይመስላል:: በሕዝብ ላይ ይኮፈሳሉ:: በመሆኑም እንበልና እንደገና የድርጅቶች ውስጣዊ ይዘት ራሱ ዴሞክራሲን በሩቁ ያለ ይመስላል:: ካባ የለበሱና በጣ የ ትነት ደረጃ የተሰየሙ ተክለሰውነታቸው የሚያደነቁር ግለሰቦች መስፈናቸው ችግር መኖሩን ጠቋሚ ነው:: በባህላችን በተለይም በቆየው ደረጃ አንድ አዛዥ አለቃ መፈለጉ የነበረ ቢሆንም በዛሬው ፖለቲካ ደረጃ ድርጅት የጋራ አመራርንና ውስጣዊ ዴሞክራሲን አስቀድሞ መገኘቱ አስፈላጊ ነው:: አንድን ወይም ሁለት ግለሰቦችን በሁሉም ከህሊናት መድቦ መጎንበሱ ከዴሞክራ ሲያዊ ድርጅቶች የሚጠበቅ አይደለም:: ዶክተር እገሌ በሚል ወይም ኮለኔል እገሌ በሚል ክብራ ቸው የማይደፈር የማይገሰስ አለቆችን መሰየሙ ሕዝብን መናቅና ዴሞክራሲንም መፃረር ነው:: የባዕድ ቋንቋ የማይናገረው፣ የፈረንጅ ወይም የሆነ ዲግሬ ተብዬና ዶክተር ወዘተ ቅፅል የሌለው፣ አፈር ገፊው ሰፊውና ብዙው ወገናችን ዛሬም ቢሆን ሀገርን ለማዳን መሰረት ነው:: ሕዝብን ያልያ ዘና ያላከበረ እንቅስቃሴ የትም አይደርስም:: የፖለቲካ ሀሁ በትግልና ሀገር ማዳን ተጋድሎ ዋና ው ተዋናይ ሕዝብ እንጂ ጥቂት ምርጥ ነን ባይ ግለሰቦች አለመሆናቸውን ያስረዳል::

ሌላው የሰለጠነ ፖለቲካ አራማጅ ነን ብለው የሚጮሁ ክፍሎች ልፈፋ የፖለቲካ ሰዎችን ዕድሜ ይመለከታል:: መለስም ይህን ዘፈን ሲያቅራራ የቆዩት ወይም ዕድሜያቸው የገፉ ለቀው ወጣቶች ይተኩ ብሎ ካለ በኋላ ይቅርታ እስከ ቀጣዩ አምስት ዓመትማ እኔም አለሁባችሁ ብሎናል:: የሰለ ጠነ ፖለቲካ ማለት የቀድሞዎቹን፣ ታግለው የተሰዉትን፣የታገሉትን ማብጠልጠል ነው የሚሉ

አሉና ያረጁ ያፈጁ ይወገዱን በጅምላ እየሰበኩ ናቸው:: እነ ኔልሰን ማንዴላ ቢያረጁም መምራታ ቸው አይታያቸውም:: ወጣት የተባሉት አፈ ምላጮች ከሀዲ ሆነው ሕዝብን ማስለቀሳቸውን ይረሳሉ:: ዋናው ጉዳይ የዕድሜ ሳይሆን የአቅዋም ነው:: የፖለቲካ ሀሁን ያላወቁ ግን ሁሌም አቢዩን ከመለስተኛው ያምታታሉና አቢይ ያልሆነውን ነጥብ ዋና አድርገው ይዘፍኑበታል:: ዛሬ የድርጅቶች ችግር መሪዎች ዕድሜያቸው መግፋቱ ሳይሆን መስመራቸው ከሕዝብ ፍላጎት ጋር አለመግጠሙ ነው:: ድርጅቶች ለዘመናት መታገላቸው ደግሞ ኃጢያት ሳይሆን ፀጋ ነው:: የደቡ ብ አፍሪካው የነማንዴላ ድርጅት የተመሰረተው በ 1912 ሲሆን ለድል የበቃው ከ 60 ዓመት በኋላ መሆኑን ማስታወስ ተገቢ ነው:: ስለዚህ ዋናው አቅዋምና እንቅስቃሴ ነው እንጂ የድርጅት መሪዎች ዕድሜ አይደለም:: ይህ ቢባልም መሪዎች መተካትና ወጣቶችም ቦታ መያዝ እንዳለባቸ ው ክርክር አያሻውም:: ድርጅቶች በርክተውና ፀንተው በመገኘታቸው እንደ ድክመት ተቆጥሮ መወገዛቸው አሳዛኝ ነው:: ድርጅትን ፀንቶ ማቆየቱ ራሱ ከባድ ትግል ነው:: ማቆየትም የሚደነቅ ነው--በተለይም ሕዝባዊ አቅዋምን ይዘው ሳያጎበድዱ:: ስንቱ ቡድን አለሁ አለሁ ብሎ ሳይውል ሳያድር ሲከስም አላየንም? ስለዚህ ዋናው ጉዳይ ማን ለሕዝብና ለሀገር ቆሟል የሚለው እንጂ ማን ዕደሜው ገፍቷል መሆን የለበትም:: የነ ስብሀት ነጋ ድርጅት ሌሎችን መሪዎቻችን አረጁ ብሎ ለመተቸት አይችልም:: ወያኔ ያልሆነ ርዕስና መወያያ ነጠብ አይስጠን::

ነገ ምርጫ በተባለው ሂደት ሕዘብ ሊነሳሳና ያልተጠበቀ ተቃውሞ ሊያሳይ ይችላል:: የሚጠበቅ ነው--ሕዝብ ሁሌም ባልጠበቅነው ያስገርማናልና:: ዱብ ዕዳ ሳይሆን “ ዱብ ደስታ ” ቢያጋጥመ ን እሰየው አብሺር የምንለው ነው:: ወያኔ ምርጫውን በተጠበቀው መሰረት አሸንፎ ከዚያም ተቃዋሚ የነበሩት ላይ ሊዘምት መቻሉም መጠበቅ አለበት:: ከዚህ ሌላ ግን ከወያኔ ምርጫ ባሻገ ርና በኋላ ምን መደረግ አለበት ለሚለው ተገቢውን ምላሽ መስጠት ደግሞ ተገቢና አስፈለጊ ነው :: ወያኔ ልዩ ልዩ ግጭቶችን በመጫር የዜጎችን ትኩረት ሊዘውር መሞከሩ አይቀርም:: የአባይን ም ጉዳይ በዚሁ ሊጠቀምበት እየጣረ ነው:: ነቅቶ ወግድ ማለት ያሻል:: ወያኔን በሚፈይድ መንገ ድ ለመታገል ምን መደረግ አለበት ለሚለው የበሰለ ምላሽ መስጠት መቻል አለብን:: የኢትዮጵያ ሕዝብ ነፃነትና ስርየት ከማንኛውም ባዕድ-- ቀረበ ራቀ -- ሊመጣ አይችልም:: 18 ዓመት አይተ ነዋል--አልሰራም:: በራሳችን ላይ መተማመን አለብን:: ነገ ለሕዝብ የሚበጅ ጊዜን ከፈለግን ዘንድ ትላንትን መርሳት አንችልም:: ታሪኩን የረሳ ስህተቱን ይደግማል ነው:: ስለዚህም ያለፈው ን ሳንረሳ፤ ዛሬንም ገምግመን ለብሩህ ነገ በሁላችን ጠላት በወያኔ አገዛዝ ላይ በጋራ እንነሳ የሚለ ው ጥሪ መሰተጋባትና ምላሽም ማግኘት አለበትና ለወሳኙ ትግል አለና እንበል::